# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 323 ሐምሌ 11 2006 ገጽ


አንብበው ያስነብቡ!
አባዝተው ያሰራጩ!

የኢትዮጵያ ወታደር ሆይ! ራስህን ተመልከት! ራስህን ታዘብ! ዛሬ ያለህበት ሁኔታ አሳፋሪ ነው። አዛዦችህ አገርን፣ ትውልድንና ታሪክን ለማጥፋት የተነሱ ናቸው። አንተን ተጠቅመው ነው ይህንን ዓላማቸውን የሚያስፈጽሙት። ይህ ላንተ ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጆችህ ውርደት ነው። ከወያኔ ባርነት ራስህን ነፃ አውጣና የነፃነት ታጋዮችን ተቀላቀል። ወያኔ መጥፋቱ አይቀርም። ወያኔ የቀድሞውን ጦር እንደበተነው አንተን ለመበተን የሚሻ የለም። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እህት በ24 ሰአታት አገር ለቀው እንዲወጡ ታዘዙ

በዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በግፍ ታስረዉ የሚሰቃዩትን ታናሽ ወንድማቸዉን ለመጠየቅ ከሚኖረበት አሜሪካ አዲስ አበባ የሄዱት የአቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ እህት ወይዘሮ ብዙአየሁ ጽጌ በአገዛዙ በተሰጣቸዉ ጥብቅ ትዕዛዝ ሃያ አራት ሰዐት በማይሞላ ግዜ ዉስጥ ኢትዮጵያን ለቅቀዉ መዉጣታቸዉ ተሰማ። የወንድማቸውን ጉዳይ ለመከታተል በሚል ከ10 ቀናት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ቢያመሩም፣ ከትናንት በስቲያ ደህንነት ጽ/ቤት ከተጠሩ በኋላ አገሪቱን በአስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ ተነግሯቸዋል። በታዘዙበት ሰአት ለመመለስ እንደሚቸገሩ የተናገሩት ወ/ሮ ብዙአየሁ፣ የ 24 ሰአት ጊዜ የጊዜ ገደብ ከተሰጣቸው በሁዋላ ዛሬ ወደ አሜሪካ ተመልሰዋል። ወ/ሮ ብዙአየሁ የአቶ አንዳርጋቸውን ቤተሰቦች በመወከል ጉዳዩን ለመከታተል በሚል መሄዳቸውን ከቤተሰቦች የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ኢህአዴግ የአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ የእግር እሳት እንደሆነበት የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። አቶ አንዳርጋቸው የህዝቡ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆናቸውና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የግንቦት7 ዝናም ከምንጊዜውም በላይ በመጨመሩ የገዢውን ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችን እያበሳጨ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽ በአገር ውስጥም በውጭም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አሁንም በተከታታይ ስልኮችን እየደወሉ አስተያየቶችን እየሰጡ ነው። በፐርዝ አውስትራሊያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ከእንግሊዝ ቆንስላ ጽህፈት ቤት ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል። ኢትዮጵያውያኑ ለቆንስላው ላቀረቡት ጥያቄ የፐርዝ የእንግሊዝ የቆንስላ ሃላፊ፣ አገራቸው የአቶ አንዳርጋቸውን ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ እየተከታተለችው ነው የሚል መልስ ሰጥተዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ስርዓቱን የሚከዱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በየቀኑ እየጨመረ መሆኑ ተነገረ

በተለያየ መልኩ የወያኔን ዘረኛ ስርዐት አናገለግልም እያሉ የመከላከያ ሠራዊቱን እየከዱ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነት መከበር የትጥቅ ትግል የሚያካሄዱ ኃይሎችን የሚቀላቀሉ ሰዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መሄዱን ሰራዊቱ ዉስጥ የሚገኙ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች በመናገር ላይ ናቸዉ። የኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥን የመከላከያ ምንጮች እንደገለጹት ባለፉት 20 ቀናት ብቻ ከባድሜ ግንባር ቁጥራቸዉ እስከ 110 የሚደርስ ወታደሮች የወያኔን ስርዐት ከድተዉ ወደ ኤርትራ እና ወደ መሃልአገር አቅንተዋል። ከ15 ቀናት በፊት በባድሜ አካባቢ ሲያጎ በተባለው ቦታ ላይ የሰፈሩ 60 የ 33ኛ ክፍለጦር አባላት በአንድ ሌሊት ሰራዊቱን ጥለው የጠፉ ሲሆን፣ ኤርትራ መድረስና አለመድረሳቸውን ለማወቅ የተደረገው ጥረት እስካሁን አልተሳካም። ወታደሮቹ የጠፉት በክፈለጦሩ የተደረገውን ግምገማ ተከትሎ ነው። ከግምገማው በሁዋላ በየቀኑ ቢያንስ 2 ሰዎች ከተለያዩ ክፍለጦሮች እየጠፉ ወደ መሃል አገርና ወደ ኤርትራ ያመራሉ።

7 አመት ያገለገሉ በርካታ የመከላከያ ሰራዊት አባላት መልቀቂያ ቢያስገቡም፣ መከላከያ ሚኒስቴር ግን ወታደሮቹን ለመልቀቅ እስካሁን ፈቃደኛ አለመሆኑንም ምንጮች ገልጸዋል። በዚህም የተነሳ በሰራዊቱ ውስጥ ያለው ውጥረት ተባብሷል። የመከለካያ ሚኒስቴር በቅርቡ በየአገሩ እየዞረ ሰራዊት ለመመልመል ያደረገውም ሙከራም የተፈለገውን ውጤት ሊያመጣ አልቻለም። ባለፈው ወር መጨረሻ ላይ የ33ኛ ክፍለጦር አባላት ከመቀሌ በተላኩት በኮሎኔል ሃጎስ ገብረማርያም መሪነት እንዲገመገሙ የተደረገ ሲሆን፣ ገምገማውን ተከትሎ ኮሎኔሉ ሃጎስ በአንድ ወታደር ተገድለዋል። ምንጮች እንደገለጹት ግምገማ ከመካሄዱ በፊት የእያንዳንዱ ወታደር ክፍል እንዲፈተሽ የተደረገ ሲሆን፣ ኢቻንግ አሊ በተባለ ከጋንቤላ አካባቢ በመጣ ወታደር ማደሪያ ክፍል ውስጥ መጽሃፍ ቅዱስ ተገኝቷል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ውጭ ጉዳይ ሚ/ር አቶ አንዳርጋቸውን ለመጎብኘት የሚመለከታቸዉ አካላት መፍቀድ አለባቸዉ አለ

የወየኔን ስርዐት ገና ከእንጪጭነቱ ጀምሮ በአንቀልባ ተሸክሞ ያሳደገዉና ዛሬም እንደ ህጻን ልጅ የሚንከባከበዉ የእንግሊዝ መንግስት ወያኔ የራሱን ዜጋ አስሮ ሲያንገላታ እንኳን ፍቱልኝ ማለት መጎበኘትም አለመቻሉ ታወቀ። በቅርቡ የእንግሊዘዝ መንግስት በዉጭ ጉዳይ መ/ቤቱ አማካይነት አተ አንዳርጋቸዉን ለመጎብኘነትና የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ በመጠየቅ ለወያኔዉ አገዛዝ የጻፈዉ ደብዳቤ አሉታዊ ምላሽ አግኝቷል። ይህንን በተመለከተ የወያኔ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ለእንግሊዝ የአፍሪካ ክፍል ሃላፊ በጻፈው ደብዳቤ፣ አቶ አንዳርጋቸው የህግና የማማከር አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ”የሚመለከታቸው አካላት” መፍቀድ አለባቸው ብሎአል። የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ”የሚመለከታቸው አካላት” ያላቸውን አካላት በስም ከመጥቀስ ተቆጥቧል። ይሁን እንጅ የመረጃው ምንጮች እንደሚሉት ”የሚመለከታቸው አካላት” የተባሉት የደህንነት ሰዎች ናቸው።

የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ይህን መልስ የጻፈው፣ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የአፍሪካ ክፍል ሃላፊ ”አቶ አንዳርጋቸውን የመጎብኘት” ፈቃድ እንዲሰጣቸው የጻፉትን ደብዳቤ ተከትሎ ነው። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በመልሱ ማዘኑንና ተጨማሪ መልስ እየጠበቀ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።የኢህአዴግ የደህንነት አባላት አቶ አንዳርጋቸው እንዳይጎበኙና የምክር አገልግሎት እንዳይሰጣቸው የሚከለክሉት፣ የአቶ አንዳርጋቸውን ስቃይ በማብዛት እና በስቃይ ውስጥ ሆነው የሚናገሩትን ለህዝቡ በማቅረብ የህዝቡን የትግል ወኔ ለመስበር መሆኑን አንድ የቤተሰባቸው አባል ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ግንቦት ሰባትን ለማዳከም የተሰራዉ ስራ ከፍተኛ ዉጤት አስገኘልኝ ብሎ ፎከረ

አንድ አንዳርጋቸዉን ይዞ በማሰሩ (ለዚያዉም በህገወጥ መንገድ ከሌላ ከሀዲ ስርዐት ጋር በመመሳጠር) አገር ዉስጥም ከአገር ዉጭም ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃዉሞ የገጠመዉ ዘረኛዉ የወያኔ ስርዐት ወያኔ ግንቦት ሰባትን ለማዳከም የተሰራዉ ስራ ከፍተኛ ዉጤት አስገኝልቶልኛል እያለ እራሱን ማፅናናት መጀመሩን ለስርዐቱ ቅርበት ያላቸዉ ምንጮቻችን በመናገር ላይ ናቸዉ። የአንዳርጋቸዉ ጽጌብ መታሰርና የህዝቡን ምላሽ አስመልክቶ ባለፈዉ ሳምንት ማብቂያ ላይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አዳራሽ የጸረ ሽብር ግብረሃይሉና የወያኔ ባለስልጣናት በጋራ የመከሩ ሲሆን፣ስኬታማ ስራዎችን ለመስራት 3 ሚልየን 400 ሺ ዶላር ወጭ ማድረጉን ገልጿል። “ኢሳያስም ቢያስፈልገን እርሱን የመያዝ አቅም ላይነን” በማለት ራሱን እንደ ማሞ ቂሎ ያሞካሸው ግብረ ሃይሉ፣ “ኢህአዴግ ንግስት ንቧን በመያዙ የቀጣዩ ምርጫ ድል በር ላይይገኛል” ሲልበሪፖርቱ አትቷል። ወያኔ ከወያኔ ጋር የሚወዳደረዉን ምርጫ አሸንፋለሁ ብሎ መናገር ምን ያህል ትርጉም የለሽ የሞኝ ስብከት መሆኑ ያልገባዉ ይህ የዘረኞችና የእንብላዉ ክምችት የሆነ አገዛዝ ህዝብ በቁጣ ተነሳስቶበት እየተመለከተ ሕዝብ ይመርጠኛል ብሎ መፎከሩ ወያኔ በስርዐት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በግልሰቦች ደረጃም ምን ያህል ደነዝ እንደሆነ ያሳያል ሲሉ አንድ በስልክ ያናገሩን ምሁር ተናግረዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የፓርላማዉ አባል ሽመልስ ከማልና እሱ የሚመራዉ የፕሬስ ድርጅት ደካማ መሆናቸዉን ተናገሩ

በወያኔዉ ፓርላማ ዉስጥ የባህል፣ ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሃን ቋሚ ኮምቴ ስብሳቢ የሆኑት ወይዘሮ ፈቲያ የሱፍ የአዲስ ዘመን፣ ኢትዮጵያ ሄራልድ ፣ በሬሳ ፣ ዓልኣለም ጋዜጦች፤ የዘመን መጽሄት አሳታሚ የሆነው በአቶ ሽመልስ ከማል የቦርድ ሰብሳቢነት የመራው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስራቸዉን በሚገባ መወጣት ያልቻሉ ከንቱ ድርጅቶች መሆናቸዉን ተናገሩ። ወይዘሮዋ ይህንን ጠንከር ያለ ትችት የሰነዘሩት በቅርቡ 73ኛ የምስረታ ዓመቱን ያከበረውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቁሙ እየሞተ መሆኑን በመጠቆም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባዉጡት ጽሁፍ ነዉ።

የቋሚ ኮምቴው ስብሳቢ ወ/ሮ ፈቲያ ዩሱፍ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ዓርብ እና ቅዳሜ እለት በታተመ ቃለ ምልልሳቸው እንደተናገሩት የአዲስ ዘመን ፣ ኢትዮጵያ ሄራልድ፣ በሬሳ፣ ዓልኣለም ጋዜጦች እና የዘመን መጽሄት አሳታሚ የሆነውና በአቶ ሽመልስ ከማል የቦርድ ሰብሳቢነት የሚመራው የኢትዮጵያ ፕሬስድርጅት ተወዳዳሪ መሆን እንዳልቻለ፣ የጋዜጦቹ ህትመት ቁጥርም ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ እንደመጣ፣ በገበያ ላይ የሚያነበው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አገራዊ ጥሪ ለመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላት

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላትን ከአለቆቻቸው ለይቶ ይመለከታል።

የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት ከፍተኛ ሹማምንት ከህወሓት የተቀዱ፣ ለህወሓት ሥልጣን የቆሙ፣ ዘረኞች፣ ፋሽስቶችና ሙሰኞች መሆናቸው በገሃድ የሚታወቅና በተደጋጋሚ ጥናቶችም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። በዘመነ ወያኔ የሠራዊት አዛዥነት ሹመት መሥፈርቶች ዘር፣ የፓለቲካ አመለካከትና ለህወሓት ያላቸው ታማኝነት ነው። በዚህም ምክንያት ሁሉም ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች የተያዙት ሙሉ በሙሉ የህወሓት አባላት በሆኑ የትግራይ ተወላጆች ነው። እነዚህ የጦርና የፓሊስ ሹማምንት ኢትዮጵያን ወረው እንደያዙት አገር ሲዘርፉ፣ ሕዝቧንም ሲገሉና ሲገርፉ እንሆ 23 ዓመታት አልፈዋል። በእነዚህ 23 ዓመታት ትግራይን ጨምሮ በደል ያልደረሰበት የኢትዮጵያ ግዛት እና የኅብረተሰብ ክፍል የለም። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእነዚህ ፋሽስቶች ተረግጧል፣ ተዋርዷል፣ ተግዟል። የንቅናቄዓችን ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያዊያን የነፃነት አርበኞች በእነዚህ እኩይ የሠራዊቱና የፓሊስ አዛዦች ሰቆቃ እየተፈፀመባቸው ነው። የወያኔ የጦርና የፓሊስ አዛዦች እና ሰላዮች አገራችን እያደሙ፤ ሕዝባችንን እያስለቀሱ ነው። በወያኔ ፋሽስት የጦርና የፓሊስ አዛዦች እና ሰላዮች ጥምረት ሰቆቃ የሚፈፀምበት የኅብረተሰብ ክፍል በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል። የወያኔ ማሰቃያዎችን የሞሉት የፓለቲካና የሀይማኖት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና ብሎገሮች መሆናቸው ለዚህ አንድ ማሳያ ነው።

የሠራዊቱ የበታች ሹማምንትና ተራ አባላት ጥንቅር ግን ከአዛዦቹ ፈጽም የተለየ ነው። የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላት ከመላው የኢትዮጵያ ግዛቶች የተውጣጡ፤ እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በነፃነት እጦት፣ በመብቶች መገፈፍ እና በኑሮ ውድነት የሚሰቃዩ ዜጎች ናቸው። የኢትዮጵያ ወታደር በወያኔ አዛዦቹ እየታዘዘ ወገኑን የሚበድል ቢሆንም ራሱ ከመበደል ግን አይድንም። የኢትዮጵያ ወታደር በወያኔ አዛገፉ ታዞ ሌላኛውን ወገኑን ቢያስርም ሹሙ ፊቱን ባዞረበት ጊዜ እራሱ ደግሞ ከመታሰር አይድንም። የኢትዮጵያ ወታደር ወያኔ አዞት ምስኪኖችን ይደበድባል፤ ራሱ ደግሞ በወያኔ ይደበደባል። የኢትዮጵያ ፓሊስ በወያኔ ትዕዛዝ ንጹሀን ዜጎችን ያስራል፣ ያሰቃያል፤ እራሱ ደግሞ በወያኔ ይታሰራል፣ ይሰቃያል። ይህ ምን የሚሉት ባርነት ነው? የወያኔ ሹማምንቶች በሚመሩት የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን በህወሓት የሚደርስባቸው በደል ሌላው ኢትዮጵያዊ ከሚደርስበት ይብስ እንደሆን እንጂ የሚያንስ አይደለም።

ግፍ መብቃት አለበት። በጥቂት የህወሓት ሹመኞች ትዕዛዝ በኢትዮጵያዊው ወታደር ላይ የሚደርሰው ውርደት ማብቃት አለበት። ሠራዊቱ የኢትዮጵያ እንጂ የህወሓት ሠራዊት አይደለም፤ ሊሆንም አይገባውም። ሠራዊቱ ለራሱ ነፃነት ብቻ ሳይሆን ለአገርና ለሕዝብ ደህንነት ዘብ የመቆም ኃላፊነት አለበት። የኢትዮጵያ ሠራዊት የህወሓት የባንዳ ሠራዊት ሆኖ ሕዝብን በማሰቃየትና ሀገርን በመበደል ተግባር ላይ ተሠማርቶ ማየት አንሻም። ይህንን ለራሱ ክብር ያለው፤ አገሩንና ሕዝቡን የሚወድ የሠራዊቱ አባልም የሚፈቅደው ጉዳይ አይደለም።

ስለሆነም ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሚከተለው ሀገራዊ ጥሪ ለመላው የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላት ያቀርባል።

ውድ የኢትዮጵያ የመከላከያ ወይም የፓሊስ ሠራዊት አባል! በጥቂት የህወሓት ፋሽስቶች መዳፍ ውስጥ ሆነህ የገዛ ራስህን፣ የቤተሰቦችህን፣ የወገንህን እና የአገርህን ስቃይ ማራዘምህን አቁም። አንተ የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ እንጂ የጥቂት ጎጠኞች ሎሌ ልትሆን አይገባም። አንተ የኢትዮጵያ ሕዝብ መከታ እንጂ የእያንዳንዱ ቤተሰብ ስጋት መሆን የለብህም። አንተ የመጪው ትውልድ አርዐያ እንጂ ሕፃናትንና ወጣቶችን ማስፈራሪያ መሆን የለብህም።

የኢትዮጵያ ወታደር ሆይ! ራስህን ተመልከት! ራስህን ታዘብ! ዛሬ ያለህበት ሁኔታ አሳፋሪ ነው። አዛዦችህ አገርን፣ ትውልድንና ታሪክን ለማጥፋት የተነሱ ናቸው። አንተን ተጠቅመው ነው ይህንን ዓላማቸውን የሚያስፈጽሙት። ይህ ላንተ ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጆችህ ውርደት ነው። ከወያኔ ባርነት ራስህን ነፃ አውጣና የነፃነት ታጋዮችን ተቀላቀል። ወያኔ መጥፋቱ አይቀርም። ወያኔ የቀድሞውን ጦር እንደበተነው አንተን ለመበተን የሚሻ የለም። አንተ ዛሬ ከወገን ጋር ወገንተኛነትህን ካሳየህ ከአገዛዙ ጋር እጠፋለሁ ብለህ አትስጋ። ለዚህም ነው አንተ ዛሬ በግልም ሆነ በቡድን የምትወስደው እርምጃ የአገራችንን ብቻ ሳይሆን የሠራዊቱን እጣ ፈንታ ይወስናል ብለን ወገናዊ ጥሪ የምናቀርብልህ።

ውድ የኢትዮጵያ የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላት ወገናችን! ከበዳዮች ጎን ሳይሆን ከተበዳዮች ጎን ቁም። ከገራፊዎችና ገዳዮች ጎን ሳይሆን ከነፃነት ታጋዮች ጎን ሁን። ዛሬውኑ ወስን። አሁን የነፃነት ታጋዮችን መቀላቀል ቀላል ሆኗል። ያሉበትን ታውቃለህ፤ ተቀላቀል። አልያም የጠመንጃህን አፈሙዝ በፋሽስት አለቆችህ ላይ አዙር። ይህንን እርምጃ በመውሰድ ከታሪክ ተወቃሽነት እራስህን በመታደግ ለአገርህና ለወገንህ አለኝታህን አረጋግጥ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የደብረ ታቦር ህዝብ በባለስልጣናት መማረራቸውን ገለጹ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚኖረዉ የደብረታቦር ከተማ ህዝብ የወያኔ አገዛዝ በተለያየ መልኩ የሚአደርስበትን መከራና ፍዳ መሸከም ያቃተዉ መሆኑን በመግለጽ ከአሁን በኋላ ለሚደረገዉ ነገር ሁሉ ትዕግስቱ ያለቀ መሆኑን ገለጸ። ህዝቡ ይህንን ቁጣዉን የገለጸዉ የደብረ ታቦር ከተማና የዞኑ አመራር ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ነዉ። እንደ ከተማዉ ነዋሪ አገላለጽ ደብረ ታቦርና ህዝቧ በመሰረተ ልማት አለመኖርና በመልካም አስተዳደር ችግር እየተሰቃዩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ይህ አለም ደጉ የተባሉ የደብረ ታቦር ኗሪ ”የጋማ ከብት እና ሰዎች በአንድ ላይ እየጠጡ መሆናቸውንና ይህም ሁኔታ ለውሃ ወለድ በሺታ እንደዳረጋቸው ተናግረዋል።አቶ ፍስሃ ይ መር የተባሉ ነዋሪ የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች ልጆቿም ያልቃሉ እሱዋም ትሞታለች እንደተባለው ኢትዩጲያም ሞታለች ደብረ ታቦርም ሞታለች በማለት የኑሮ ውድነት የፈጠረውን ጫና ተናግረዋል ያምሮት አሰፋ የተባሉ እናት ደግሞ” እኔን የሚበድለኝ የቀበሌ ሹም ነው። እኔ ገንዘብ እንዳልሰጥ፣ ቢራ እንዳላጠጣ ድሃ ነን፤ ካርታ እና ፕላን እያለኝ ለባለሃበት የሚፈርድ መንግስት በመሆኑ መሬቴን ተቀምቻለሁ ብለዋል። በደቡብ ጎንደር ዞን ደብረታቦር ከተማ የሚዲያ አካላት በተገኙበት የከተማው እና የዞኑ አመራር ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ አቶ ሲሳይነው ተስፋ የተባሉ ኗሪ“24 ሰዓታት የመንቀሳቀስ መብት የለንም፣ ከምሺቱ ሶሰስት ሰዓት በኃላ በልዩ ሃይል ፖሊስ እንደበደባለን። መለሰ አካደሚ እና ፋውንዴሺን ከአበል እና ከደሞዝ እየተጠቆረጠ በግዴታ ያለፍላጉታችን ይወሰድብናል። ይህንንም ያልፈፀመ አሸባሪ ይባላል” ሲሉ ተናግረዋል። ብአዴን በአማራ ክልል የተለያዩ ቦታዎች ለሚቀጥለው ምርጫ እንዲደራው ህዝቡን እያወያየ ቢሆንም፣ ህዝቡ ግን በስርአቱ መማረሩን ከመግለጽ አልተቆጠበም።

## የፓርላማዉ አባል ሽመልስ ከማልና እሱ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንደሌለ በመጥቀስ በይፋ ድክመቱን ተናግረዋል። ድርጅቱ ችግሩን ለመቅረፍ ወደ ኮርፖሬት አደረጃጀት እንዲገባ በተደጋጋሚ እንደ ተነገረው ነገርግን በማኔጅመንቱ ድክመት እንዳልተሳካ ተናግረዋል። «አምና ሪፎርም ውስጥ ግቡ ብለናቸው የሆነ ነገር ጀምረው እኛ ሥራ በዝቶብን ወደሌላ ዘወር ስንል ይተውታል» በማለት የማኔጅመንቱን እንዝህላልነት አሳይተዋል። ሠራተኛው ገሚሱ በሲቪል ሰርቪስ፣ አንዳንዱ በቦርድ እንደሚተዳደርና ይህ ልዩነት በኮርፖሬት አደረጃጀት እንዲስተካከል ተነግሮአቸውም እንዳላስተካከሉት ወ/ሮ ፈቲያ ገልጸዋል።

## ምናምንቴዎች በሠለጠኑ ግዜ ህዝብ ያልቀሳል !!!

ኢትዮጵያ ላይ ጥቂት ምናምንቴዎች ሰልጥነው ህዝቡን እያስለቀሱት ነው። ኢትዮጵያዊያን ለብዙ ዘመን በብዙ ሃዘንና እንባ ውስጥ መኖራቸው የታወቀ ነው። የአሁኑ ሃዘን እንዲሁ ተራ ሃዘን፤ ልቅሶውም ተራ ልቅሶ አይደለም። መራር ሮሮ እንጂ። ይህን የህዝብ ሮሮ የሚሰማ መንግስታዊ አካልም የለም። በ“Global terrorist database” ውስጥ የሥም ዝርዝሩ ተመዝግቦ የሚገኘው “የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ” ነኝ የሚለው ቡድን መንግስ ነኝ ቢልም የመንግስት መልክና ባህሪይ ሊኖረው አልቻለም። ህወሃት መንግስታዊ አሸባሪ እንጂ የኢትዮጵያ መንግስት ለመሆን የሞራልም ሆነ የእውቀት ብቃት ያለው ቡድን አይደለም።

ህወሃት ከተፈጠረ ጀምሮ የብዙ ንፁህ ዜጎችን ደም አፍሷል። ብዙ ዜጎችን ለስቃይ እና ለስደት ዳርጓል። ብዙ ቤተሰብን በትኗል። በተለይ ጠላቴ ነው ብሎ የሚያምነውን የአማራ ህዝብ ለማጥፋት ሴቶችን መካን የሚያደርግ ክትባት እስከ መከተብ ደርሷል። በዚህም የአማራው ቁጥር ከነበረው ቀንሶ ተገኝቷል። ይህ አሸባሪ ቡድን በኦጋዴን፤ በአፋርና በጋምቤላ የፈፀመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ዓለም ያወቀው ነው። በኦሮሚያ የፈሰሰው የንፁሃን ዜጎች ደም ከምድር ወደ ሰማይ እየጮኸ ነው። በአዲስ አበባ እና በደቡብ የተበተነውን የቤተሰብ ብዛት ቆጥረን አንዘልቀውም። በትግራይ የሚገኙ ምርጥ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አልቀዋል። የተረፉ ጥቂቶች ቢገኙም መግቢያ መውጪያ አጥተው በሁለት ሰይፍ የሚቆረጡ ሁነዋል።

የትግራይ ነፃ አውጪዎች ያተረፉልን ነገር ቢኖር ውርደት ነው። ውረድቱ የከበዳቸው ዜጎች ራሳቸውን በእሳት አቃጥለዋል። ገደል ውስጥ ራሳቸውን ወርውረው የሞቱም አሉ። ህወሃቶች ባሉበት ከምንኖር ብለው ስደተን መርጠው የበርሃ ንዳድ፤ የባህር ዐዞ እራት የሆኑ ብዙ ናቸው። በባእዳን አገር ውስጥም ማረፊያ አጥተው የሚንከራተቱም ቁጥራችው በቀላል የሚገመት አይደለም። ይህ የህወሃት መራር ፍሬ ነው።

አዎን በአገራችን ላይ እነዚህ እግዜርን የማያውቁ የሰይጣን ድንኳኖች ከሰለጠኑ ዘመን ጀምሮ የንፁህ ሰው ደም ሳይፈስ የዋለበት ቀን የለም። ህወሃቶች የትልቁንም የትንሹንም ደም በማፈሰስ የሚረኩ፤ ቤተሰብንም በትነው ድሃ አደግ በማድረጋቸው የሚደሰቱ ፍጡራን ስለመሆናቸው የእስከዛሬው ምግባራቸው ቋሚ ምስክር ነው። ለስልጣን ካላቸው ሥሥት የተነሳም ከባዕዳን ጋር እየተመሳጠሩና ብዙ ሚሊዮን ገንዘብ እየከፈሉ ነፍሰ ገዳዮችንና አፋኞችን ቀጥረው ዜጎችን እስከማሳፈን ደርሰዋል። የዚህ ዕኩይ ተግባር ሰለባዎች ብዙ ናቸው። ታላቁ ሰው አንዳርጋቸው ፅጌ የዚህ እኩይ ተግባር ሰለባ ከሆኑ ብዙ ኢትዮጵያዊያን መካከል አንዱ ነው።

ጠላቶቻችን(ህወሃቶች) እና ወዳጆቻችን በሙሉ ስሙን ! አንዳርጋቸው የተነሳው :

- *ሚዛኑን ስቶ መሳለቂያ የሆነው ፍትህ ወደ ሚዛኑ ለመመለስና ፍጹም የህግ የበላይነትን በአገራችን ለማስፈን ነው።*
- *የነፃነት ትርጉም ሳይገባው ስለነፃነት ሊነግረን ሳይሆን የነፃነትን ጣዕም አጣጥሞና ተርድቶ ከምር ኢትዮጵያዊያን ያለፍርሃት በነፃነት እንዲኖሩ ለማስቻል ነው።*
- *ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነው፤ ብዙሃኑም ጥቂቶቹን ተሸከመው መከራቸው በዝቶ የሚኖሩበት ሥርዓት ተወግዶ ሁሉም ዜጎች በእኩልነት እንዲኖሩ ለማደረግ ነው።*
- *ጠባብ ጎሰኛነት ተወግዶ ሁሉም በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ በሠላም መኖር የሚችልበት ንፁህ አገር እንድትኖረን ለማድረግ ነው።*
- *ከዚያች ድሃ አገር ላይ እየዘረፈ በውጭ አገራት ባንኮች ውስጥ የሚደብቅ ይሄን ማድረግ ካልቻለም መሬት ምሶ የዘረፈውን ገንዘብ የሚቀብር ዘራፊ ቡድን ሳይሆን ያለውን ሁሉ ለአገሩና ለህዝቡ ለመስጠት ከልቡ ያመነ መሪ አገሪቷን የሚመራበት ሥርዓት እንዲዘረጋ ለማድረግ ነው።*
- *ኢትዮጵያችን በውሸታሞች፤ ለህዝባቸው ክብር በሌላቸው፤ህዝባቸውን በሚንቁ፤ ከራሳቸውው ፍላጎት ውጪ ሌላ ወገን ህዝብ ማለትን በማያውቁ ደካሞች መገዛቷ አክትሞ ህዝቡን ፈርቶና አክብሮ የሚመራ፤ ህዝብ ላይ የሚጫን ሳይሆን በህዝብ የተመረጠና የተወደደ መሪ እንዲኖራት ለማብቃት ነው።*

ግንቦት ሰባትንና መሪውን አንዳርጋቸው ፅጌን በህወሃቶች ዘንድ አሸባሪ እንዲሆኑ ያደረጓቸው እነዚህ ከላይ ለመዘርዘር የሞከርናቸው ቁም ነገሮች ናቸው እንጂ እንደ ህወሃቶች ግንቦት ሰባት ባንክ ሲዘርፍ፤ የእምነት ሥፍራዎችን ሲያወድም፤ ትምህርት ቤቶችን ሲያፈራርስ፤ የቀደመው ትውልድ በደምና አጥንቱ ያቆየውን ድንበር ቆርሶ ሲሸጥ፤ የአገሪቷን ለም መሬት ለባእዳን ሲሸጥ፤ አንዱን ጎሳ ከሌላው ጋር አጋጭቶ ደም እንዲፈስ ሲያደርግ ተገኝቶ አይደለም።

ባንክ መዝረፍ፤ የእምነት አምባዎችን ማርከስ፤ ትምህርት ቤቶችን ማውደም፤ የአገሪቷን ድንበር እያፈርሱ ለባዕዳን አሳልፎ መስጠት፤ ለም መሬቶችን ለባዕዳን መቸብቸብ፤ በህዝቦች መካከል ጥላቻን መዝራት፤ ከድሃ ጉሮሮ ላይ ሠርቆ በውጪ አገራት ባንኮች ውስጥ ገንዘብ ማጠራቀም ህወቶች እንደ ሙያ የተያያዙት የእለት ተዕለት ተግባራቸው ነው። ግንቦት ሰባት የተነሳው እንዲህ ዓይነት ነውረኞችን ከተቆናጠጡበት የስልጣን ወንበር ላይ አውርዶ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያዊያን የምትሆን አገር እንድትሆን ለማድረግ ነው። የመሪያችን የአንዳርጋቸው ፅጌም ምኞት ይሄው ነው። ኢትዮጵያን ከጥቂት ዘረኞችና ዘራፊዎች እጅ አውጥቶ የብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ አገር እንድትሆን ማድረግ።

ይሄ የኢትዮጵያ ውድ ልጅ በነውረኞቹ የትግራይ ነፃ አውጪዎች እጅ ገብቷል። ነፃ አውጪ ነን ባዮቹ አንበሳውን ከበው ለመቦጫጨቅ እንደሚያጓሩ ጅቦች ዓይናቸውን አጉረጥርጠው እያሰቃዩት ይገኛሉ። ምንም እንኳ ይሄ ታላቅ ሰው በነፍሰ ገዳዮቹ እጅ ቢወድቅም እርሱ የጀመረው የነፃነት ጥያቄ የሚሊየኖች ጥያቄ ሆኖ ከመቸው ግዜ በላይ ሚሊየኖችን አስነስቷል። በዓለም ዙሪያ “እኔም አንዳርጋቸው ነኝ፤ እኔም ግንቦት ሰባት ነኝ” የሚሉ ድምፆች ከፍ ብለው እየተሰሙ ነው። አንዳርጋቸውን ማሰር እንጂ እርሱ የጀመረወን የነፃነት ጥያቄ፤ እርሱ የዘረጋውን የትግል መስመር ማሰር አይቻልም። ለዚህም ነው አንዳርጋቸው የማይጨበጥ ፅኑ መንፈስ ነው የሚባለው።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ህወሃት የተባለው ዘረኛ እና የወሮበላዎች ቡድን የገነባው የሰይጣን ድንኳን ፈርሶ ፍትህ፤ነፃነት እና እውነተኛ ዴሞክራሲ ተገንብቶ እስከሚያይ ድረስ የጀመረውን ሁለ ገብ ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል።

የተከበራችሁ ያገራችን ዜጎች ሆይ ስሙን ! እኔም አንዳርጋቸው ነኝ ማለታችሁ አንድ በጎ እርምጃ ነው። እኔም አንዳርጋቸው ነኝ ማለት አንዳርጋቸው ራሱን አሳልፎ ለሰጠው ድንቅ ዓላማ ራሳን አሳልፎ መስጠት ማለት መሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል። አንዳርጋቸው የቆመለትን ዓላማ ለማስፈፀም እኛ ወደ እናንተ እሰከምንመጣ መጠበቅ የለባችሁም። በያላችሁበት አምስትም ስድስትም አስርም እየሆናችሁ የአርበኝነት ተግባር መፈፀም መጀመር አለባችሁ። የቀደመዉ ትውልድ ፋሽት ጣሊያንን በየመንደሩ እየተደራጀ እና የጎበዝ አለቃ እየመረጠ መፋለሙን አስታወሱ። እናንተም ከምታምኑት ጋር እየተደራጃችሁና የጎበዝ አለቃ እየመረጣችሁ የዘመኑን ፋሽስት ልትፋለሙት ይገባል። ዘመቻ አንዳርጋቸው ማለት እኔ ለነፃነቴ፤ እኔ ለፍትህ እና ለህግ የበላይነት፤ እኔ ከዘረኞቹና ከሌቦቹ ህወሃቶች የፀዳች አገር ለመፍጠር ተነስቼአለሁ ማለት ነው። ለዚህም ዓላማ ለመሞትና ለመግደል ዝግጁ ነኝ ልትሉ ግዜው አሁን ነው። እንደ ቀድሞ ዝም ብላችሁ የምትሞቱ ሳትሆኑ ለመግደልም የምትችሉ መሆኑን በተግባር ማሳየት መቻል አለባችሁ።

“ትግሬን ነፃ” እናወጣለን ብላችሁ የተነሳችሁ እናንተ ነውረኞች ሆይ ስሙ ዓይናችሁ እያየ፤ ጆሯችሁም እየሰማ ከወገኖቻችን ጎን ሁነንና እጅ ለእጅ ተያይዘን ልትገነቡ የሞከራችሁትን የዘረኝነትና የዝሪፍያ መረብ እንበጣጥሰዋለን። እናንተ ዘረኞችና ዘራፊዎች ስሙ! ህዝብን እንዳስለቀስዋችሁ መቀጠል እንደማትችሉ እርግጠኛ ሁኑ። አገራችን ኢትዮጵያም እናንተን ከመሰሉ ምናምንቴዎች ፀድታ ህዝቦቿም በነፃነት የሚኖሩበት ግዜ እሩቅ አይደለም። ያን ግዜ በእናንተ ነውሮኞች ግፍ የሚያለቅስ ህዝብ አይኖርም። አበቃን!!!

**ድል ለኢትዮጵያችን ይሁን !!!!**

## የአማራ አርሶ አደሮችን ትጥቅ የማስፈታት ሂደቱ ሂደት ከፍተኛ ችግር ገጠመዉ

ከትግርኛ ተናጋሪዉ ዉጭ የሌላዉ ክልል ህዝብ በተለይ አማራዉ ትጥቅ ሲታጠቅ አይኑን የሚያመዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የአማራ ገበሬዎች እራሳቸዉን ለመከላከል የታጠቁትን መሳሪያ ለማስፈታት ያደረጉዉ ጥረት ከፍተኛ ተቃዉሞ የገጠመዉ ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚዉን ጎራ እያጠናከረዉ መሆኑን የአገር ቤት ዘጋቢዎቻችን አንዳንድ ከፍተኛ የስርዐቱን ባለስልጣኖች በመጥቀስ የላኩልን ዜና ያሰረዳል። በያዝነዉ ው መግቢያ ላያ የአስተዳደር ፀጥታና የፖሊስ ኮሚሺን በጋራ የ2006 ዓ.ምኢ የአስራ አንድ ወራት የስራ አፃፀም በገመገሙበት ውይይት የጎጃም፤ የጎንደር፤ የሸዋና የኦሮሞ አርሶ አደሮች ዛሬም በድብቅ መሳሪያዎችን በነፍስ ወከፍ በየቤቱ ይዘው እንደሚገኙ ያወሱ ሲሆን፣ አርሶ አደሩ የጦር መሳሪያውን እንዲመልስ ጥረት ቢደረግም አልተሳካም ብለዋል። ወያኔ በከፍተኛ ደረጃ ይደግፈኛል ወይም በስርዐቱ ላይ ከፍተኛ እምነት አለዉ የሚለዉንና በተለይም በቅርቡ በረከት ስምኦን ሁን ያልነዉን ሁሉ ይሆንልናል ያለዉን የኢትዮጵያን ገበሬ ለምን እንደሚፈራና እራሱን የሚከላከልበትን መሳሪያ ለምን እንዳይይዝ እንደፈለገ ግልጽ ነገር የለም፤ ሆኖም መሬት ላይ ያሉ መረጃዎች ሁሉ የሚያሳዩት የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ኃይሎች በአንድ አቅጣጫ ሰብረዉ ከገቡ ገበረዉ ሙሉ ለሙሉ ከነመሳሪያዉ ይቀላቀላቸዋል የሚል ከፍተኛ ስጋት በያኔ ዘንድ እንዳለ ግልጽ ነዉ።

አዲስ ህግ እንዲወጣ የጠየቁት የፀጥታሃይሎች አርሶ አደሩ በህገወጥ እጅ የተሰገሰገው ከ 4 ሚሊዩን በላይ የሚገመት የተለያየ የጦርመሳሪያ በአገሪቱ ለሚፈጸም ግድያ ዋና መንስኤ መሆኑን አመልክተዋል። በዘመቻ የጦር መሳሪያ ማስፈታት እና የቅጣት ወሰን መመሪያ እንደሃገር አለመኖር ችግር መሆኑን በማንሳት የፌደራል መንግስት የህገወጥ መሳሪያ ቁጥጥር አዋጅ እንዲያወጣ በሪፖርታቸው ጠይቀዋል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ያናገርናቸዉ አንድ የህግ አዋቂ ምሁር ኢትዮጵያ ዉስጥ ዋና ዋና የግድያ ምክንያቶች ስርዐቱ የተዋቀረበት የዘር ክልል እንጂ ጠመንጃና ሽጉጥ ግድያ ለመፈጸም ሰዎች የሚጠቀሙባቸዉ መሳሪያዎች አንጂ በራሳቸዉ የግድያ ምክንያት አይደሉም ሊሆኑም አይችሉም ብለዋል።

## ፍርደ ገምድሉ የወያኔ ፍርድ ቤት ጦማሪያኑና ጋዜጠኞን ወነጀለ

ሰላማዊ ዜጎችን ከየቤታቸዉና ከስራ ቦታቸዉ አፍሶ ካሰረ በኋላ ባለፉት ሁለት ወራት ማስረጃ ሲሰበስብ የከረመዉ የወያኔዉ ተላላኪ በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩት ጦማሪያን፣ ሶልያና ሽመልስ (በሌለችበት)፣ በፍቃዱ ኃይሉ፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ ማህሌት ፋንታሁን፣ አጥናፉ ብርሃኔ፣ ዘለዓለም ክብረት፣ አቤል ዋበላ፣ እንዲሁም ጋዜጠኞቹ አስማማው ኃይለ ጊዮርጊስ፣ ኤዶም ካሣዬና ተስፋለም ወልደየስ ላይ ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም. ጥፋተኛ ናችሁና ክሳችሁን ተከላከሉ የሚል ብይን ሰጠ። ተጠርጣሪዎቹ የሽብርተኝነት ወንጀል በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተሳታፊ በመሆን ለአመፅ ተግባር በህቡዕ መደራጀታቸውን፣ የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት ያቀረበው የክስ ቻርጅ ይገልጻል።

እንደ ዓቃቤ ሕግ ክስ ተጠርጣሪዎቹ በህቡዕ በመደራጀት፣ የአጭርና የቅርብ ጊዜ ግብ በማቀድና በመንደፍ ከግንቦት 2004 ዓ.ም. ጀምሮ እጃቸው እስከተያዘበት ጊዜ ድረስ በፓርላማ ሽብርተኛ ተብለው ከተሰየሙት የግንቦት 7 እና የኦነግ ድርጅቶች መመርያና ሐሳብ ሲቀበሉ መቆየታቸው ተገልጿል። ከተጠርጣሪዎቹ አንዷ የሆነችው ሶሊያና ሽመልስ የቡድኑ መሥራችና አስተባባሪ በመሆን ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም. መቆየቷና ከ2006 ዓ.ም. ጀምሮ በውጭ አገር አስተባባሪና የውጭ ግንኙነት ሆና ከመሥራቷም በተጨማሪ፣ ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ተልዕኮ በመቀበል፣ አባላትን በማደራጀትና በመመልመል ስትሠራ መቆየቷን ክሱ ያስረዳል። የህቡዕ ቡድኑ ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም. ‹‹ሴኩሪቲ ኢን ቦክስ›› የተባለ ሥልጠና እንዲሠለጥንና እንዲደራጅ ስትመራ መቆየቷም በክሱ ተካቷል።

ጋዜጠኞቹም ሆኑ ጦማሪያኑ የሚሰሩትና የሰሯቸዉ ስራዎች በግልጽ የሚታዩ ሆነዉ ሳለ ወያኔን ሰለተቃወሙ ብቻ ከያሉበት ተሰብስበዉ ከታሰሩ በኋላ ሁለት ወር ሙሉ ወያኔያዊ መረጃ ለመስብሰብ ከፍተኛ ሙከራ ቢደረግም አልተሳካም። ሆኖም ማሰር; መክሰስና መወንጀል የማይሰለቸዉ ወያኔ እንደለመደዉ በብዕራቸዉ የሚቃወሙትንና እንኳን የግንቦታ 7 አባል ሆነዉ ሊሰሩ ስለ ግንቦት 7 ጽፈዉ የማያዉቁትን ዜጎች በራሱ ቋንቋ ሽብርተኞች ናችሁ ብሎ ወንጅሏቸዋል። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎቸ አልገባቸዉም እንጂ እሱ የሚዋጋዉ ሽብርተኝነትን ሳይሆን ነጻነትንና ፍትህን ነዉ። ለዚህም ነዉ አንደ ግንቦት 7 ፍትህ፤ ነጻነትና ዲሞክራሲ ብለዉ የተነሱ ወገኖችን በሙሉ ሽብርተኛ ናችሁ እያለ የሚያስረዉ።

ሌላኛው ተጠርጣሪ በፍቃዱ ኃይሉ የአገር ውስጥ የሽብር ቡድንን በመምራትና የሥራ ክፍፍል በማድረግ፣ እንዲሁም ግብ በማስቀመጥና ስትራቴጂ በመንደፍ ከሽብርተኛ ኃይሎች ጋር ግንኙነት ሲፈጥር መቆየቱ በክሱ ተጠቅሷል። የዓቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው ከሆነ ተጠርጣሪ ናትናኤል ፈለቀ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ካልተያዙ ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን የህቡዕ ድርጅቱ የአገር ውስጥ አስተባባሪ በመሆን በሥሩ ላሉት አባላት የሥራ ክፍፍል መመርያ በመስጠት፣ ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት በመፍጠር መመርያ ከመቀበሉ በተጨማሪ፣ ለአመፅ ተግባር የሚውል የተላከለትን 48,000 ብር ማከፋፈሉንም ክሱ ያብራራል።

ሌሎቹ ተጠርጣሪዎች በህቡዕ ድርጅቱ ውስጥ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ መሥራችና አባል በመሆን የግንቦት 7 እና የኦነግን ስትራቴጂና ዕቅድ በመቀበል በውጭና በአገር ውስጥ ባሉ የቡድኑ አባላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ በውጭና በአገር ውስጥ ሥልጠና በመውሰድ፣ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም በማቀድ፣ በመዘጋጀት፣ በማሰርና በማነሳሳት ወንጀል መከሰሳቸውን ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው ክስ ያስረዳል።በሁሉም ተጠርጣሪዎች ላይ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው ሁለተኛ ክስ እንደሚያስረዳው ተጠርጣሪዎቹ በወንጀሉና በሚያስገኘው ውጤት ተስማምተው በሕገ መንግሥት ሥርዓት የተቋቋመን መንግሥት በአመፅ፣ በሁከትና በብጥብጥ ለመለወጥ በማሰብ ከግንቦት 2004 ዓ.ም. እስከተያዙበት ዕለት ድረስ በህቡዕ ተደራጅተው፣ የሥራ ክፍፍል በመፍጠር፣ ሥልጠናዎችን በመውሰድ፣ አመፅ የሚቀሰቅሱ ጽሑፎችን በመበተን፣ የአመፅ ቡድኖችን በማደራጀት ሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በአመፅና በሁከት ለመለወጥ በመሞከር ወንጀል መከሰሳቸውን የዓቃቤ ሕግ ክስ ያስረዳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጋዜጠኞቹና ጦማሪያኑ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ የምርመራ መዝገቡ መዘጋቱ ፍጹም መረን የለቀቀ ሕገወጥ አካሄድ ነዉ ሲሉ የታሳሪዎቹ ጠበቃ አማረሩ። በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በክስ ላይ የሚገኙት ሦስት ጋዜጠኞችና ስድስት ጦማርያን ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ፖሊስ ‹‹ምርመራዬን ስለጨረስኩ መዝገቡ ይዘጋልኝ›› በማለት መዝገቡ እንዲዘጋ ማድረጉ ሕጉን ያልተከተለና አደገኛ መሆኑን ጠበቃቸው አስታወቁ። በበበተጠርጣሪ ጋዜጠኞች ተስፋለም ወልደየስ፣ አስማማው ኃይለ ጊዮርጊስ፣ ኤዶም ካሳዬና ጦማሪያንና የሕግ መምህር ዘለዓለም ክብረት፣ ናትናኤል ፈለቀና አጥናፉ ብርሃኔ ሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የሚቀርቡበት ዕለት ነበር። እንደወትሮው ሁሉ የተጠርጣሪዎች ቤተሰቦች፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጠኞች፣ ጓደኞቻቸውና የተለያዩ የችሎት ታዳሚዎች በጠዋት ማልደው በፍርድ ቤት ግቢ የተገኙ ቢሆንም፣ እስከ ቀኑ 5፡30 ሰዓት ድረስ ፖሊስም ሆነ ተጠርጣሪዎቹ ወደ ችሎቱ አልመጡም። ከ5፡30 ሰዓት በኋላ ሌሎች ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተጠርጣሪዎቹና ፖሊስ ችሎት ቆይተው ሲወጡ፣ የተጠርጣሪዎቹ ጠበቃ አቶ አመሐ መኮንን፣ ደንበኞቻቸው ፍርድ ቤት መቅረብ አለመቅረባቸውን ለማጣራት የዕለቱን ተረኛ ዳኛ ለማነጋገር ገቡ። ጠበቃው ስለደንበኞቻቸው ፍርድ ቤቱን ሲጠይቁ፣ ፖሊስ ምርመራውን መጨረሱን በማሳወቅ መዝገቡ እንዲዘጋለት ጠይቆ መዘጋቱን ሲያስረዳቸው፣ ‹‹እንዴትና በምን ሁኔታ?›› የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡም፣ ከመዘጋቱ ውጪ ምንም ምላሽ ሊያገኙ አለመቻላቸውን ተናግረዋል።

እስረኛ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የምርመራ መዝገቡ ሊዘጋ እንደማይችል የሚናገሩት ጠበቃ አመሐ፣ ተጠርጣሪዎቹ ከሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በእስር ላይ መሆናቸው፣ በሕግ አግባብ በፍርድ ቤት ምንም ትዕዛዝ ባልተሰጠበት ሁኔታ በመሆኑ ድርጊቱ ሕገወጥና አደገኛ መሆኑንም አስረድተዋል።ፖሊስ ምርመራውን ካጠናቀቀ ተጠርጣሪዎቹን ፍርድ ቤት ይዞ በመቅረብ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳትና ክስ እስከሚመሠረትባቸው ድረስ በዋስ እንዲቆዩ ወይም የሕግ ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት ስለሚቆዩበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት እንደነበረበት አስረድተዋል።ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ባልሰጠበት ሁኔታ ተጠርጣሪዎቹ ባሁኑ ወቅት የት እንዳሉ እንደማይታወቅ የሚናገሩት ጠበቃው፣ በወንጀል ሕጉና በሕገ መንግሥቱ በተጠሰው አካልን ነፃ የማውጣት መብት (ሐቢየስ ኮርፐስ) ክስ ሊመሠርቱ እንደሚችሉ ገልጸዋል። በሌላ የምርመራ መዝገብ የተካተቱት ጦማሪያን ማህሌት ፋንታሁን፣ አቤል ዋበላና በፈቃዱ ኃይሉ ደግሞ ፍርድ ቤት መቅረብ የነበረባቸው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ፍርደ ገምድሉ የወያኔ ፍርድ ቤት ጦማሪያኑና

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

ሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. የነበረ ቢሆንም፣ ተጠርጣሪዎቹም ሆኑ መርማሪ ፖሊስ ሳይቀርቡ መቅረታቸውን ጠበቃው ጠቁመዋል።

ዘጠኙም ተጠርጣሪዎች ‹‹የሙብት ተሟጋች ነን›› ከሚሉ የውጭ ኃይሎች ጋር በሙሉ ሐሳብና ገንዘብ በመስማማት ሕዝብን የማተራመስ፣ አገርንና መንግሥትን የማፍረስ ዘገባ በኢንተርኔትና በተለያዩ ድረ ገጾች ያልሆነ መረጃ ሲያስተላልፉ ተገኝተዋል በሚል ፖሊስ ሚያዝያ 17 እና 18 ቀን 2006 ዓ.ም. በቁጥጥር ሥር እንዳዋላቸው መዘገባችን ይታወሳል። ፖሊስ በተጠርጣሪዎቹ ላይ ለሁለት ጊዜ የ14 ቀናት የምርመራ ጊዜ ጠይቆ ከተፈቀደለት በኋላ፣ በሦስተኛው የፍርድ ቤት ቀጠሮ የተጠርጣሪዎቹ ጉዳይ ውስብስብና ድርጊቱም የሽብርተኝነት ድርጊት መሆኑን በመጥቀስ፣ ለተጨማሪ ምርመራ 28 ቀን እንዲፈቀድለት የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን በመጥቀስ ተፈቅዶለት መመርመር ላይ መሆኑን መዘገባችን አይዘነጋም። ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ሥር ከዋሉ 78 ቀናት ሞልቷቸዋል።

## የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እህት በ24 ሰአታት አገር ለቀው

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሱዳን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለኢሳት በላኩት ደብዳቤ የአቶ አንዳርጋቸው መታፈን ”ወያኔ ፍጹም አወሪነቱን ያሳየበት እና ዘላአለም የነጻነት ታጋዮችን ለማስፈራራት እና ከትግሎ ሜዳ ለማስውጣት የተጠቀመበት የትእቤት ስራ ነው።” መሆኑን ያሳያል ካሉ በኋላ፣ የተወሰደው እርምጃ ህዝቡን ለትግል እንደሚያነሳሰው ገልጸዋል። በሌላ ዜና ደግሞ በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሰው ማእከላዊ እስር ቤት እንዲታሰሩ የተደረጉት የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ሀብታሙ አያሌው፣ የድርጅቱ የድርጅት ጉዳይ ምክትል ሃላፊ አቶ ዳንኤል ሽበሺ፣ የሰማያዊ ፓርቲ ምክትል የምክር ቤት ሰብሳቤ አቶ የሽዋስ አሰፋ እንዲሁም አረና ፓርቲ የስራ አስፈጻሚና ታዋቂ ጸሃፊ መምህር አብርሃ ደስታ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ ተብሎ ቢጠበቅም፣ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ቀርተዋል። አንድነት ፓርቲ የተያዙት ሰዎች በ48 ሰአታት ውስጥ ፍርድ ቤት አለመቅረባቸውን በመግለጽ ክስ መስርቶ ነበር። ይሁን እንጅ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎታል።

## ስርዓቱን የሚክዱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ወታደር ኢቻንግ መጽሀፍ ቅዱስ ለምን እንዳስገና ሲጠየቅ፣ “አባቴ እንደማስታወሻ የሰጠኝ ነው” በማለት የመለሰ ሲሆን፣ ገምጋሚው ኮሎኔል ሃጎስ ግን ” ይሄ የውትድርና ቦታ እንጅ የሃይማኖት ቦታ አይደለም፣ መጽሃፍ ቅዱስክን ከካምፕ ውስጥ አስወጣ” ብሎ ትእዛዝ ሰጥቷል። ወታደር ኢቻንግም መጽሃፍ ቅዱሱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑና ይህን ካላደረገም እንደሚታሰር በማወቁ፣ ኮሎኔሉ ለእረፍት እንደወጣ መሳሪያውን ከክፍሉ ይዞ በመምጣት በጥይት ደብድቦ ገድሎታል።

ወታደር ኢቻንግ ግድያውን ከፈጸመ በኋላ በገዛ መሳሪያው ራሱን አጥፍቷል። በግምገማው ወቅት ከፍተኛ ትችት የተሰነዘረባቸው 60 የሰራዊቱ አባላት ኮሎኔል ሃጎስ በተገደሉበት እለት፣ ሌሊቱን ተመካክረው በአንድ ጊዜ መጥፋታቸውን ምንጮች አክለው ገልጸዋል። በባድሜ አካባቢ ያለው እስር ቤት ዋጠው እየተባለ የሚጠራ ሲሆን፣ ጎንና ጎኑ በድንጋይ ተሰርቶ ከስር ስሚንቶ፣ ከስሚንቶው ስር ደግሞ ውሃ እንዳለውና እስረኞችን በቅዝቀዜ ለመቅጣት ተብሎ መዘጋጀቱን ለማወቅ ትቸሎአል። እስረኛ ወታደሮች ቀኑን ሙሉ ብርሃን ሳያዩ በካቴና እንደታሰሩ እንደሚገረፉ የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል። በሰራዊቱ ውስጥ እየጨመረ የመጣው ተቃውሞ ያሰጋው መንግስት የደሞዝ ጭማሪ እንደሚያደርግ ቃል በመግባት ለማረጋጋት ቢሞክርም፣ ሰራዊቱ ግን አስተዳዳራዊ በደሎችንና በሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ዘረኝነት በመጥላት፣ የደሞዝ ማማለያውን ባለመቀበል ጥሎ እየጠፋ ሲሆን አንዳንድ ወታደሮች ደግሞ መልቀቂያቸው ከዛሬ ነገ ይደርሳል በማለት በተስፋ እየተጠባበቁ እንደሚገኙ መረጃው አመልክቷል።

ወታደራዊ አዛዦች በአዲስ አበባና በተለያዩ የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች የገነቡዋቸው ዘመናዊ ህንጻዎችና ያካበቱት የሃብት መጠን በሰራዊቱ ውስጥ ተደጋግሞ የሚነሳ ሲሆን፣ በተለይ ከህወሃት ውጭ ያሉ አንዳንድ የአማራ እና የኦሮሞ ወታደሮች አመጽ ሊያስነሱ ይችላሉ ተብሎ በመጠርጠራቸው ልዩ ክትትል እንደሚደረግባቸው ምንጮች ገልጸዋል። የጋምቤላ ተወላጅ የሰራዊቱ አባላትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ታማኝነታቸውን እያጎደሉ ነው በሚል በአንዳንዶች ላይ ልዩ ክትትል እየተደረገባቸው ነው። አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል ለአባይ ግድብ ማሰሪያ፣ ለመለስ ፋውንዴሽንና ለሌሎችም የክፍያ ትእዛዞች ገንዘብ ከከፈለ በሁዋላ ተቆራርጦ የሚደርሰው ክፍያ ወር እስከ ወር አያደርሰውም። በአንጻሩ ነባር ታጋዮች የሚባሉት የህወሃት ጄኔራሎች በመቶ ሚሊዮኖች ብር የሚቆጠር ህንጻዎችን ገንብተው በማከራየት ላይ መሆናቸው ይታወቃል።

የየረር ባሪዉ ግጭት የሰዉ ህይወት ቀጠፈ ሰዉ በላዉ የወያኔ ስርዐት የህዝብን ጥያቄ ማስተናገድ ተስኖት በሰላማዊ መንግድ የሚቃወመዉን ሁሉ እያሰረ ማሰር ዋነኛዉ ስራዉ በሆነበት በአሁኑ ወቅት ከወራት በፊት በየረር ባሪ ጎሳዎች የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ ከታሰሩት 19 አገር ሽማግሌዎች መካከል 2ቱ በእስር ቤት ውስጥ ማረፋቸውን በስፍራዉ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን የላኩልን ዜና ያስረዳል። ንጹህ ዜጎች በግፍ እስር ላይ እንዳሉ ህይወታቸዉ ማለፉ ሳይንስ የማረሚያ ቤት ሃላፊዎች የሟቾችን አስከሬን ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ሟቾቹን በራሳቸው ጊዜ በመቅበራቸው የብሄረሰቡ ተወላጆች ከፍተኛ ተቃውሞ አስነስተዋል።

ተቃውሞውን በሃይል ለመጨፍለቅ የክልሉ ፕሬዚዳንት ልዩሚሊሺያዎችን ወደ አካባቢው በመላክ ላይ እያሉ፣ ከአዲስ አበባ በተላለፈ ትእዛዝ የመከላከያ ሰራዊቱ ፈጥኖ በመንቀሳቀስ ልዩ ሚሊሺያውን አግቶ አስቁሞታል። ሚሊሺያውምወደ ጅጅጋ እንዲመለስ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል። ይክልሉ ፕሬዚዳንት አቶ አብዲ ሙሃመድ፣ እርሳቸው የሚያዙት ሚሊሺያ በመከላከያ ሰራዊት አዛዦች ትእዛዝ ወደ መጣበት እንዲመለሱ መደረጋቸው ያበሳጫቸው ሲሆን፣ እስካሁን ግን ይህ ነው የሚል መልስ አልሰጡም። በክልሉ ፕሬዚዳንትና በተለይም በደህንነት ሚኒስትሩ ጌታቸው አሰፋ መካከል የተፈጠረው ልዩነት እርስ በርስ እስከ መዘላለፍና መካሰስ አድርሷቸዋል። አቶ አብዲ የክልሉን የደህንነት ሃላፊ የህወሃቱን መቶ አለቃ አወጣሃኘን ካሰሩ በሁዋላ ልዩነቱ እየሰፋ ሄዷል። አቶ አብዲም በቅርቡ የአገር ሽማግሌዎችን ሰብስበው ከእንግዲህ የደህንነት ሃይሎችን እንዳይፈሩዋቸው፣ በክልሉ ያሉት ብቸኛ ሰው እርሳቸው መሆናቸውን መናገራቸውን መዘገባችን ይታወቃል።የህወሃት ገብረመስቀል ይደገፋሉ። ይሁን እንጅ በቅርቡ አልሸባብ ኦጋዴን ውስጥ ገብቶ 33 የኢትዮጵያ ወታደሮችን መግደሉን ተከትሎ የመከላከያና የአገር ውስጥ የደህንነት ሃይሉ ፣ ጣታቸውን በአቶ አብዲ ላይ መቀሰር ጀምረዋል።

## ውጭ ጉዳይ ሚ/ር አቶ አንዳርጋቸውን ለመጎብኘት የሚመለከታቸዉ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ገልጸው፣ ይህንንም የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እንዲያውቀው ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱት መረጃዎች እንደሚያሳዩት አቶ አንዳርጋቸውን በእንቅልፍ እጦት በመቅጣትና የተለያዩ የስነ ልቦና ጫናዎች እንዲደርሱባቸው በማድረግ የማይፈለጉትን ነገር እንዲናገሩ ግፊት እያደረጉባቸው ነው። እስካሁን ድረስ የሚደርስባቸውን ከፍተኛ ስቃይ ተቋቁመው ምንም አይነት መረጃ ባለመስጠታቸው የተበሳጩት የጸረ ሽብር ግብረሃይል የሚባለው ቡድን መሪዎች በአቶ አንዳርጋቸው ላይ ተጨማሪ የማሰቃያዘዴዎች እንዲፈጸሙ ባለፈው ቅዳሜ በጠ/ሚንስትር ግቢ በተካሄደው ስብሰባ ውሳኔ አሳልፈዋል።

የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትም ሆነ የአቶ ሃይለማርያም ጽህፈት ቤት ለቀረበለት የጉብኝት ጥያቄ መልስ አለመስጠቱ፣ የአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ ከጀርባ ሆነው አገሪቱን በሚገዙት ጥቂት ሰዎች እጅ መውደቁን ያሳያልበማለት ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ሰው ተናግረዋል። በተመሳሳይ ዜና ደግሞ ህዝቡ አሁንም በአቶ አንዳርጋቸው መታሰር የተሰማውን ቁጭት እየገለጸ ነው። በጃፓን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንዲሁ የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል።